የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ
የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ፕሮግራም
441 4th Street, N.W., Suite 570N
Washington, D.C. 20001
Teléfono: (202) 727-4559; Fax: (202) 727-9589

# የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ፕሮግራም መረጃ

የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ

## የዲ.ሲ. የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ድንጋጌ ምንድን ነው?

በ2004 የተደነገገው የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ድንጋጌ በከንቲባ አንቶኒ ኤ. ዊሊያምስ በሚያዝያ 21 2004 ጸድቋል፤ ድንጋጌውም የወጣው ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ወይም መጠነኛ ችሎታ (LEP/NEP) ላላቸው የኮሎምቢያ ወረዳ ነዋሪች በሕዝብ ግልጋሎቶች፤ ፕሮግራሞች፤ እና እንቅስቃሴች የበለጠ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፣፣

ድንጋጌው የወረዳው መንግስት ፕሮግራሞችን፤ መሥሪያ ቤቶችን፤ ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ግልጋሎት ሰጪችን የሚከተሉትን አራት ነገሮች እንዲፈጽሙ ያዛል፣፣

- የአስተርጓሚ አስፈላጊነትን መመልከት እና የቃል ትርጉም ግልጋሎት ማቅረብ፣፣
- ጠቃሚ ለሆኑ ሰነዶች እንግሊዘኛ ወደአልሆነው ቋንቋ የጽሁፍ ትርጉም ግልጋሎት ማቅረብ፤ ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ወይም መጠነኛ ችሎታ (LEP/NEP) ያላቸው የሕዝብ ብዛት 3% ወይም 500 ግለሰቦች ሆነው ሲገኙ፤ ከሁለቱ አንሶ የተገኘው ይመረጣል፤ ግልጋሎት ከሚያገኙት ወይም ግንኙነት ከሚያደርጉት፤ ወይም ወደፊት ግልጋሎት ሊያገኙ ወይም ግንኙነት ሊያገኙ ከሚችሉት መሃከል፣፣
- የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ እቅድ ማውጣት እና ማስፈጸም፣፣
- የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ አስተባባሪ መመደብ፣፣

*ምንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ወይም መጠነኛ ችሎታ ላላቸው የኮሎምቢያ ወረዳ ነዋሪች በሕዝብ ግልጋሎቶች፤ ፕሮግራሞች፤ እና እንቅስቃሴች የበለጠ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣፣*
*ዲ. ሲ. ድንጋጌ 15-414*

የኮሎምቢያ ወረዳ ምክር ቤት የሚከተሉትን አምስት ቋንቋች በወረዳው መንግስት በብዛት ግልጋሎት የሚሰጥባቸው ናቸው ብሎ ለይቷቸዋል፤ ስፓኒሽኛ፤ ቻይኒኛ፤ ቬትናሚኛ፤ ኮሪያንኛ፤ እና አማርኛ፣፣

ድንጋጌው አንቀጾቹ «ሥራ ላይ የሚውሉበትን ደረጃ» ጠብቀው እንዲፈጸሙ ያዛልነ ይህም ማለት ከወረዳው የመንግስት ፕሮግራሞች፤ ከመሥሪያ ቤቶች፤ ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ግልጋሎት ሰጪች በድንጋጌው ውስጥ በዝርዝር ተጠቅሰዋል በእያንዳንዱ ሒሳባዊ ዓመት ከሚያዚያ 21 2004 ጀምሮ አንቀጾቹን  እንዲያከናውኑ፣፣

የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ (OHR) የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ድንጋጌን እንዲቆጣጠር በድንጋጌው ሥልጣን ተሰጥቶታል፤ (OHR) የበላይ ማስተባበርን እና የቴክኒካል እርዳታችን ለመንግስት ፕሮግራሞች፤ ለመሥሪያ ቤቶች፤ ለከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ግልጋሎት ሰጪ ይሰጣልነ በተጨማሪም የቋንቋ ግልጋሎት ማግኘትን አስመልክቶ (OHR) የሕዝብ ብሶቶችን ለመከታተል፤ ለመመልከት፤ እና ለመመርመር ሥልጣን አለው፣፣

የኮሎምቢያ ወረዳ የሰብዓዊ መብት ቢሮ (OHR) ከከንቲባው የላቲኖ ጉዳይ ቢሮ (OLA)፣ ከከንቲባው የእሲያውያን እና የፓሲፊክ ደሴቶች ጉዳይ ቢሮ (OAPIA)፣ እና የቋንቋ ግልጋሎት ማግኛ ቅንኝትነ ስደተኞችን ከሚደግፉ ሕብረተሰብ ውስጥ ናሉ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ናላቸው ጋር አብሮ ይሰራል፣፣

## ድንጋጌው «ሥራ ላይ የሚውልበት ደረጃ»

ድንጋጌው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በተግባር የሚያውሉ፣

- የጤና መስሪያ ቤት
- የሕዝብ ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የሠራተኛ ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የከተማ ፓሊስ መስሪያ ቤት
- የኮሎምቢያ ወረዳ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
- የእቅድ ጽሕፈት ቤት
- የእሳት እና የአስቸኳይ የጤና ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የሰብዓዊ መብት ቢሮ

ድንጋጌውን ከጥቅምት 1 2004 ጀምሮ በተግባር የሚያውሉ፣

- የቤት እና የሕብረተሰብ ልማት መስሪያ ቤት
- የአእምሮ ጤና መስሪያ ቤት
- የተሽከርንሪ መኪናች መስሪያ ቤት
- የልጆች እና የቤተሰቦች ግልጋሎት ድርጅት
- የአልኮል መጠጦች መቆጣጠሪያ አስተዳደር
- የተጠቃሚች እና የመቆጣጠሪያ ጉዳይ መስሪያ ቤት

ድንጋጌውን ከጥቅምት 1 2005 ጀምሮ በተግባር የሚያውሉ፣

- የመናፈሻ እና የመዝናኛ መስሪያ ቤት
- የአዛውንቶች ቢሮ
- የኮሎምቢያ ወረዳ የሕዝብ መጻሕፍት ቤት
- የሠራተኛ ጉዳይ ቢሮ
- የመዋዋያ እና የምልመላ ቢሮ
- የማረሚያ መስሪያ ቤት
- የሕዝብ ግልጋሎት መስሪያ ቤት
- የቀረጥ እና የገቢ ቢሮ

ድንጋጌው ከጥቅምት 1 2006 ጀምሮ የቀሩት ሌሎች ክፍሎችን ያንተታል፣